
# በኮሎምቢያ ከተማ ስለሚገነባው የመኪና ማቆሚያ ቦታ በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች - ንግድ

የሲያትል ከተማ የትራንስፖርት ቢሮ (SDOT) በከተማው ጎዳናዎች ስላሉት የመኪና ማቆሚያዎች እና የትራፊክ ፍሰቶችን ይቆጣጠራል። SDOT በኮሎምቢያ ከተማ ውስጥ በሬይነር ጎዳና አከባቢ እና የከተማው አጠገብ ላይ ያለውን የመኪና ማቆሚያ ቦታ ለውጥ በተመለከተ ፕሮፖዛል አቅርቦ ነበር። የፕሮፖዛሉ ዝርዝር መረጃ በጎዳና ደረጃ ምን እንደሚመስል በካርታው ላይ ማየት ይቻላል።

## በዚሁ አከባቢ የሚኖሩ ሠራተኞች የቀረበውን ፕሮፖዛል ተከትሎ ወደ ሥራ መጓዝ የሚችሉት እንዴት ነው?

- አንዳንዶቹ ሠራተኞች ምናልባት በትራንስፖርት ሊጠቀሙ ይችላሉ። በሥራ ቀናት ላይ ከ5 ሰዓት እስከ 1 ሰዓት ድረስ በቀላል ባቡር መጠቀም ይቻላል። በተጨማሪም አከባቢው ላይ የባቡር መሥመሮች ያሉ ሲሆን ቁጥራቸውም 7፤ 9፤ 50 እና 106 ናቸው። አንዳንዶቹ ሠራተኞች ለORCA LIFT ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ይህም በኪንግ ካውንቲ ሜትሮ፤ በሳውንድ ትራንዚት ሊንክ ቀላል ባቡር እና በሌሎች የአከባቢው መጓጓዣ ላይ የ50% ቅናሽ አለው።
- ከዚህ በታች በተገለፁት ቦታዎች ላይ መኪና መንዳትና ማቆም ይችላሉ፡-
    - በ29ኛው የRPZ አከባቢ ላይ መኪናዎ ያቁሙ። ፕሮፖዛል በቀረበበት የውስን መኪና ማቆሚያ ዞን (RPZ) ማስፋፊያ አከባቢ የሚገኙ ንግድ ቤቶች በተመለከተ አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው የRPZ ፈቃድ ሊገዙላቸው ይችላሉ። ይህም አከባቢ Rainier Ave S እና በS Dawson St እና በS Angeline St. ላይ የሚገኙ የጐን ጎዳናዎች የሚያካትት ነው። በአሁኑ ወቅት የፈቃዱ ዋጋ $65 ነው፤ ይህም ለሁለት ዓመት የሚቆይ ፈቃድ ነው። የማመልከቻ ቅፁ መሞላትና በንግድ ቤት ባለቤቶቹ ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻቸው ሊፈረም ይገባዋል። ይህንን የተመለከተ መረጃ www.seattle.gov/transportation/parking/lightrail_biz.htm ላይ ይገኛል። የSDOT የRPZ ፈቃድ ማዕከልን ወደ 206-684-5086 በመደወል ማግኘት ይቻላል።
    - በወየሩ ወይም በየቀኑ፤ ከጎዳናው ራቅ ብሎ የግል የመኪና ማቆሚያ ቦታ ሊገኝ ይችላል
    - ውስንነት የሌለው የመኪና ማቆሚያ አከባቢ። ከኮሎምቢያ ከተማ የንግድ አውራጃ ውጭ ከ2-3 ብሎክ ራቅ ባለ ቦታ ላይ የመኪና ማቆሚያ ለውጥ እንዲደረግ ፕሮፖዛል አልቀረበም። በእነዚህ አከባቢዎች በአብዛኞቹ ላይ የሚገኝ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ላይ ማቆም በጊዜ ወይም በሌላ መመሪያ ‘ያልተወሰነ’ ይሆናል። በአሁኑ ወቅት ያሉት የመኪና ማቆሚያ መመሪያዎች በሲያትል ከተማ ካርታ ላይ ሊገኙ ይችላሉ፡- http://web6.seattle.gov/sdot/seattleparkingmap/ ይጎብኙ።




የቀረቡ ለውጦች

- ክፍያ፡ በሰዓት 1$፤ ከ8 AM – 8 PM ከሰኞ-ቅዳሜ፤, 2 ሰዓት ገደብ (80 ቦታዎች)
- RPZ, ከጠዋቱ 7 AM-እስከ ምሽቱ 6PM, ከሰኞ-አርብ, 2 ሰአታት ከፈቃድ ውጪ(390 ቦታዎች)
- የማይከፈልበት ሰዓት ገደቦች፤ 2 ሰዓት ከ ሰኞ- ቅዳሜ ከ7 AM – 6 PM (40 ቦታዎች)
- ማቆሚያ የለም ምልክት ማቆም
- የተሽከርካሪ መሄጃ ስፍራዎችን ማቋቋም
- ከ5 PM – 2 AM ብቻ አንድን ስፍራ ለተሳፋሪዎች መጫኛነት መለወጥ
- አዲስ RPZ 29 የማቆሚያ ቦታ ይጨምሩ

Seattle Department of Transportation

## ይህ ጉዳይ ደንበኞች/ጎብኚዎች መኪናቸውን የሚያቆሙበትን ቦታ የሚነካው እንዴት ነው?

- የመኪና ማቆሚያ ለውጥ (የጊዜ ውስንነት እና የሚከፈልባቸው መኪና ማቆሚያዎች ጭማሪ) ይበልጥ የመኪና ማቆሚያ ቦታ እንዲገኝና በንግድ አውራጃው የሚገኙ ቦታዎች አከባቢ ላይ ለደንበኞች እንዲሁም ለጎብኚዎች ምቹነት እንዲጨምር ስለተደረገ የገንዘብ ገቢውም ከፍ እንዲል ረድቷል። የቀረበው ፕሮፖዛል በጊዜ ውስንነት ላይ የነበሩትን በኮሎምቢያ ከተማ መሐል ላይ ያሉት 80 ቦታዎችን ወደሚከፈልበት የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ እንዲቀየር አድርጓል። የጊዜ ውስንነቱ ለ2 ሰዓት የሚቆይ ይሆናል፥ ከምሽቱ 11 ሰዓት ላይ ለ3 ሰዓት የሚቆይ ፈቃድ መግዛት ይቻላል። የመጀመሪያው ክፍያ ለሰዓት $1 ይሆናል፥ ዋጋዎቹም ከጠዋቱ 2 ሰዓት እስከ ማታ 2 ሰዓት ላይ የሚቆይ እና ከሰኞ እስከ ቅዳሜ የሚዘልቅ ነው። ከሬይነር ውጭ እስከ አንድ ብሎክ ድረስ በነፃ መኪና ማቆም ይቻላል።

## የክብደት ዞን ለውጥ በተመለከተ መጠየቅ የምችለው ወይም ሌላ አስተያየትና ያሳሰበኝን ጉዳይ በዝርዝር መግለፅ የምችለው እንዴት ነው?

- ኢንተርነት ላይ www.surveymonkey.com/r/SDOTCC ውስጥ የሚገኘውን መጠየቂያ እስከ የካቲት 27, 2017 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ጨርሰው ይመልሱት።
- ወደ Columbiacityparking@seattle.gov በመፃፍ ወይም ወደ 206-733-9026 በመደወል ከኛ ጋር ይገናኙ።

## ቀጥሎ የሚሆነው ነገር ምንድን ነው?

- SDOT በሚያዚያ 2017 አከባቢ ስለ መኪና ማቆሚያው በተመለከተ የመጨረሻውን ዕቅዱን ለማውጣት አቅዷል፥ ይህ ዕቅድ ከወጣበት ጊዜ ማለትም ከሚያዝያ 2017 ትንሽ ወራት ቆይቶ ተግባራዊ ይሆናል።